# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ( ኢሕአፓ)

Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)

ሚያዝያ 30/2000 ዓ. ም.

## አስቸኳይ መግለጫና ጥሪ ለኢትዮጵያውያን በሞላ

## የሀገር መሬት ለባዕድ ሲሰጥ ዝምታ ወንጀል ነው

የመለስ ዜናዊ አገዛዝ የኢትዮጵያን መሬት ለሱዳን አሳልፎ መስጠቱ የተረጋገጠ ሀቅ በመሆኑ ይህ ክህደት ሲፈፀምና ወንጀሉ በተካሄደበት አካባቢ ያሉ ኢትዮጵያውያንም ላይ አደጋ እየደረሰ ባለበት ሁኔታ በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ሀገር ነዋሪ የሆነው ዜጋ ባለው አቅም ሁሉ ተቃውሞውን ማሰማት እንዳለበት ኢሕአፓ ዳግም አሰችኳይ ጥሪ ያስተላልፋል፡፡ ይህ የኢትዮጵያን መሬት ለሱዳን አሳልፎ የሰጠ የወያኔ ከሀዲ አገዛዝ ከዓመታት በፊት ይህን የክህደት ሰነድ ከሱዳን ጋር መፈራረሙን ወይም ሊፈራረም መስማማቱን የሱዳን ባለሥልጣኖች በጊዜው ያረጋገጡ ሲሆን የአዋሳኙ የገዳሪፍ ጠቅላይ ግዛት ገዢ ደግሞ ደጋግሞ ለሱዳን አራሾች ያበሰረው ዜና ነበር፡፡

በቅርቡ ደግሞ በወያኔው አገዛዝ መሪ በመለስና ኋላም ከፍተኛ ባለሥልጣኑ በአዲሱ ለገሰ የተመራ ቡድን ከሱዳን ባለሥልጣኖች ጋር ተገናኝቶ፤ ሱዳን የሀገራችንን መሬት ልትወስድ እንደምትችል መለስ ዜናዊ መወሰኑን በነገራቸው መሰረት የሱዳን ወታደሮች ሽንፋን ወንዝ ተሻግረው በቋራ በኩል እስከ ነፍሶ ገበያ ተራራ ያለውን መሬት በቁጥጥር ሥር አውለዋል፡፡ የኢትዮጵያ አርሶ አደሮችንም ወደ ሽንፋ ወንዝ እንዳይጠጉ ከማገዳቸው ባሻገር የተወሰኑ መንደሮችንም ማቃጠላቸው ታውቋል፡፡ ወደ ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያም ተመሳሳይ ሁኔታ መፈፀሙ ተነግሯል፡፡ የኢትዮጵያውያንን ተቃውሞ በተመለከተ አዲሱ ለገስ የዕድገት ፊልም ብሎ በሽህዲ (ሽህዲ በጎንደር ክ/ሀገር ከመተማ አጠገብ ያለች ትንሽ ከተማ ነች) ከተማ ለሕዝብ ባሳየበት ወቅት ሱዳን የያዘውን መሬት በዘመናዊ መንገድ አርሶ ለኢትዮጵያ ከፍተኛ የግብር ክፍያ ያደርጋል እንጂ መሬቱ አልተሰጣቸውም ብሎ ሊቀጥፍ ሲሞክር ሕዝቡ ወግድ እንዳለውም ተዘግቧል፡፡ የወያኔ አገዛዝ የኢትዮጵያን መሬት፤ በስንት ጀግኖች ደም የተከበረውን መሬት ለሱዳን አሳልፎ መስጠቱ በአሁኑ ጊዜ የተረጋጋጠ ነው፡፡

በመሆኑም አለምንም ቾልታ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሁሉ ባለው አቅምና መንገድ ተቃውሞውን ማሰማትና መሬቱን ማስከበር አለበት፡፡ ኢሕአፓ/ሠ ቋራን ይቆጣጠር በነበረበት ወቅት ተመሳሳይ የሱዳን ጥቃት ገና በታሰበበት ወቅት የቋራን ሕዝብ ብቻ ሳይሆን እስከ ደልጊና አገው ምድር ወዘተ ያለውን ሕዝብ አነሳስቶና ሕዝቡም ጉዳዩን ከሰማ በኋላ በራሱም ተነሳስቶ ብዙ ሺ የታጠቀ ሕዝብን ወደ ድንብር በመትመም የሱዳንን ዕቅድ አክሽፎት ነበር፡፡ ዛሬም ምንም እንኳን መንግሥት ነኝ ብሎ አዲስ አበባ የተሰየመው የወያኔ ቡድን ፀረ ኢትዮጵያና ከሀዲ ቢሆንም ኢትዮጵያውያን ይህንን የመሬት ቅሚያ ለማስቆም አሁንም ሊዋደቁ ይገባቸዋል፡፡ በዚህም ረገድ ፤

- በውጭ ሀገር ያሉ ኢትዮጵያውያን የፖለቲካ ልዩነታቸውን ወደ ጎን በመተው በያሉበት በመተባባር በወያኔ ኤምባሲዎችና በሱዳን ኤምባሲዎች ላይ የተቃወሞ ሰልፍ ማድረግና ይህንኑም በዓለም አቀፍ ደረጃ ማስተጋባት ይገባቸዋል፡፡ ይህ ጉዳይ ሁሉን ኢትዮጵያዊ የሚመለከትና የሚከነክንም ነውና አለምንም ቾልታ በአሰቸኳይ በዓለም አቀፍ ደረጃ ይከናወን ዘንድ ኢሕአፓ ጥሪ ያደርጋል፤ በዝግጅቱም ከሁሉም ኢትዮጵያውያን ጋር ለመተባበር ዝግጁነቱን ይገልፃል፡፡

- በሀገር ቤት ያለው ዜጋ በመላ ኢትዮጵያ ደረጃ የሀገሩ መሬት ለባዕድ በጠረራ ፀሀይ ሲሸጥ በዝምታ ማሳለፍ የለበትምና ተቃውሞውን ማሰማት መቻል አለበት፡፡ ያልተፈቀዱ ሰልፎችን ማድረግ እንደሚቻል በልዩ ልዩ ጊዜና በቅርቡም ቢሆን የታየ ነውና በዚህ አቢይ ሀገርን በሚመለከት ጉዳይ ከተቃውሞ ሰልፍ እስከ የሙት ከተማ አድማና ሌሎችንም አድማዎችና ተቃውሞዎች ለማሰማትና ለማሰተጋባት ቆርጦ መነሳት አለበት፡፡

- የጎንደር ሕዝብ በአጠቃላይና የተቀሙ መሬቶች አካባቢ ያለው ሕዝብ በተለይ በጎበዝ አለቃ ደረጃ እየተሰባሰበ ይህንን ወረራ ለመቋቋም መነሳት አለበት፡፡ በኢትዮጵያ መሬት ላይ የሰፈረን የባዕድ ጦርና ተቀጥላ ሁሉ ማጥቃት የዜጋ ግዴታ ነውና መሬት ቀምተው በሰላም ሊያርሱ ሊኖሩ እንደማይችሉ በገቢር ማሳየት ያስፈልጋል፡፡

- በወያኔ ጦር ሰራዊት ውስጥ የተሰለፉና በተለይም በጎንደር የሰፈሩ ኮሮች አባል የሆኑት ወታደሮችም የመለስ ዜናዊ ቡድን ታማኝ አባሎች እስካልሆኑ ድረስ ባገዛዙ ላይ እንዲያምፁና ይህን የክህደት እርምጃ እንዲቃወሙ በስልት መቀስቀስ ያስፈልጋል፡፡

የሀገራችንን መሬት ለባዕድ ሲሸጥ በዝምታ ማየት ወንጀል ነው!!

በጋራ ተነስተን የሀገራችንን መሬት እናስከብር!!

የሀገር ድንበርና መሬት መደፈሩን በሁሉም መንገድ እንቃወም!!

EPRP
P.O.Box 73337
Washington DC, 20056
USA
Tel. 202-291-4217 Fax 202-291-7645

E-mail : ESPIC@aol.com
Website: www.EPRP.com

EPRP
BP 22
Bois colombes 92270
France